በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣ ቅድሚያ
ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር

# የአስር ቀን የአየር ሁኔታ ግምገማ እና ትንበያ መጽሔት

## ከፌብርዋሪ 1-10/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ እንዲሁም

## ከፌብርዋሪ 11-20፤21-29/2024

## የሚኖረው የአየር ሁኔታ ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ

ፌብርዋሪ 11/2024

አዲስ አበባ

ስልክ +251115538394 ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

**ርዕስ** **ገፅ**

እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 1 እስከ 10/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ.......- 1 -
ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 1 እስከ 10/2024 .......- 3 -
ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ.......- 3 -
ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 1 እስከ 10/2024 .......- 3 -
ድረስ ዝናብ የዘነበባቸዉ ቀናት .......- 3 -
ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 1 እስከ 10/2024 ድረስ የነበረዉ.......- 3 -
የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር .......- 3 -
ምስል 1 የቀኑ ከፍተኛ የሙቀት መጠን በዲ.ሴ.......- 4 -
እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 1 እስከ 10/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርና ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ .......- 4 -
ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 1 እስከ 10/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ.......- 5 -
እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 1 እስከ 10/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ ..- 5 -
ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 1 እስከ 10/2024 .......- 5 -
ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ.......- 5 -
እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 11 እስከ 20/2024 የሚኖረው የአየር.......- 6 -
ሁኔታ ትንበያ .......- 6 -
ካርታ 6 እ.ኤ.አ. ከፌብርዋሪ 11-20, 2024 የሚኖረዉ ከፍተኛ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ.......- 7 -
ካርታ 7 እ.ኤ.አ. ከፌብርዋሪ 11-20, 2024 የሚኖረዉ  የዝናብ መጠን በሚ.ሜ .......- 7 -
እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 21 እስከ 29/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ ትንበያ.......- 7 -
ካርታ 8፡ እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 21-29፣ 2024 የሚኖረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ.......- 8 -
እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 11 እስከ 20/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ.......- 8 -
እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 11 እስከ 20/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ በዉሀዉ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ.......- 9 -



ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 1 እስከ 10/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ

ባለፉት አስር ቀናት በአብዛኛዉ የሀገርቱ አከባቢዎች ላይ ጠንካራ የደመና ሽፋን እና ክምችት ነበራቸው፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ በደቡብ፣ ደቡብ ምዕራብ፣ መካከለኛዉ፣ ምዕራብ እንዲሁም በሰሜን እና ሰሜን ምስራቅ የአገሪቱ ክፍሎች በብዙ ቦታዎቻቸዉ ላይ ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ ተመዝግበዋል፡፡ ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ከተመዘገበባቸው የሚቲዎሮሎጂ ጣቢያዎች መካከል በአዲስ አበባ ቦሌ 14.0፣ በሀዋሳ 5.0 እና 7.1፣ በደብረ ማርቆስ 3.2 እና 24.4፣ በቢሾፍቱ 30.0፣ በጎሬ 2.4፣ 1.4፣ 3.5፣ 17.8፣ 16.5 እና 1.7፤ በጅማ 37.1፣ 2.7፣ 3.5፣ 2.1፤ በነቀምቴ 6.1፣ በአቦምሳ 8.8፣19.5፤ በአዲስ አበባ ጥቁር አንበሳ 32.5 እና 3.3፤ በአይራ 13.2፤ በአለም ተፈሪ 1.4፣15.6 እና 3.6፤ በአልጌ 6.0፣24.0 እና 15.0፤ በአማን 5.1 እና 3.1፤ በአምባ ማሪያም 6.8 እና 1.5፤ በአምቦ 3.5፣2.0 እና 5.0፤ አንገር ጉቲን 10.0፣2.6 እና 6.8፤ በአርጆ 8.4፤18.6፣22.8 እና 25.8፤ በባቲ 17.0፣ በበደሌ 6.4፣7.9፣45.0 እና 29.7፤ በብላቴ 1.3 እና 22.2፤ በቦሬ 2.9፤ በቡኢ 6.0፣ በቡሬ 6.5፤ በቡረጂ 10.7፣ በኮምቦልቻ 10.6፣ በቻግኒ 1.5፤በጨፉ 16.5፣ በጭራ 16.6፣ 3.1፣4.7፣21.1፣2.3 እና 5.5፤ በዳንግላ 2.5 እና 1.6፤ በደብረ ብረሃን 1.8 እና 5.4፤ በደብረ ታቦር 10.1፤ በደብረወርቅ 1.3፤ በዲላ 3.0 እና 10.6፤ በኢጃጂ 11.7፣14.4 እና 1.0፤ በእንዋሪ 4.5፤ በፍቼ 1.4፤1.0፣4.6 እና 7.0፤ በጋቲራ 26.7፣ 21.0፣ 28.4፣ 25.6፣ 35.8፤ በግዮን 4.4፤ በጊምቢ 9.6፣2.9 ፤ በጉንዶ መስቀል 4.5፤ በሆሳዕና 1.5፣ 3.8 እና 4.5፤ በእምድብር 5.3፣11.1፤ በጂንካ 3.6፣17.2 እና 7.0፤ በካቺሴ 16.0፣5.4 እና 10.7፤ በቁሉምሳ 29.8፣ በላሊበላ 2.7፣3.1፣9.5 እና 3.2፤ በሊሙገነት 40.0፣2.0፣1.8 እና 3.0፤ በመሃል ሜዳ 29.0 በማይጨው 0.7 እና 1.2፤ በማጀቴ 1.5፤ በማጂ 70.5፣8.7፣8.5 እና 15.0፤በማሻ 57.5፣1.6፣30.2 እና 12.0፤በሚኤሶ 6.0፣በአዳማ 22.9፣ በሞያሌ 2.5፤ በንፋስ መውጫ 4.7፣5.5 እና 20.7፤ በሳውላ 4.2 እና 17.6፤ በሰኮሩ 2.7፣2.4 እና 4.3፤ በሻምቡ 14.7 እና 1.2፤ በሲርንቃ 5.6 እና 2.3፤ በቴፒ 1.6፣ 4.7፣1.4 እና 3.9፤ በተርጫ 1.5፣14.8 እና 3.5፤ በወገልጤና 15.0 እና 6.3፤ በወራቤ 1.6 እና 3.9፤- በወረኢሉ 1.4 እና 16.4፣ በባቱ 16.3 እንዲሁም በየትኖራ 1.5 በሚ.ሜ. ይገኙበታል፡፡




ስልክ +251115538394 ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ ቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል፤ የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል፤ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ፤የሲዳማ ክልል እና የምዕራብ ኦሮሚያ ክልል ዞኖች ላይ ከ31-136 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ5-8 ቀናት ያህል የነበራቸው ሲሆን፤ ከኦሮሚያ ክልል ምስራቅ እና ምዕራብ ሀረርጌ፣ ባሌ እና ምስራቅ ባሌ፣ አርሲ እና ምዕራብ አርሲ፣ ቦረና እና ሁሉም የሸዋ ዞኖች፤ ከአማራ ክልል ሰሜን፣ ማዕካላዊ እና ደቡብ ጎንደር፣ አዊ ዞን፣ ምስራቅ እና ምዕራብ ጎጃም፣ ሰሜን እና ደቡብ ወሎ፣ ዋህግምራ፣ ሰሜን ሸዋ፤ ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል መተከል እና አሶሳ ዞኖች፤ ሁሉም የጋምቤላ ክልል ዞኖች፣ ከአፋር ክልል ዞን 2፤4፣1 እና 5፤ ከሱማሌ ክልል ሲቲ፣ ሊበን እና ዳዋ ዞኖች፤ ከትግራይ ክልል ምስራቅ፣ ደቡብ እና ደቡብ ምዕራብ ዞኖች እንዲሁም አዲስ አበባን ጨምሮ ከ5-25 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ1-3 ቀናት ያህል ነበራቸው (ካርታ 1 እና 2) ፡፡


ባለፉት አስራ ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር ከኦሮሚያ ክልል ምስራቅ እና ምዕራብ ወለጋ፣ ቄለም ወለጋ፣ ቡኖ በደሌ፣ ኢሉባቦር፣ ጅማ፣ ሆሮ ጉድሩ፣ ሁሉም የሸዋ ዞኖች፤ ከአማራ ክልል ዋህግምራ፣ ሰሜን እና ደቡብ ወሎ፣ ማዕከላዊ እና ደቡብ ጎንደር፣ ምስራቅ እና ምዕራብ ጎጃም፣ የኦሮሚያ ልዩ ዞን፣ አዊ ዞን፣ ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል አሶሳ እና ካማሺ ዞኖች፤ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ጉራጌ፣ ሀዲያ፣ ሀላባ፣ የየም ልዩ ዞን፣ ከምባታ፣ ጠምባሮ፤ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ጎፋ፣ ባስኬቶ፣ ጋሞ፣ ደራሼ፣ ደቡብ ኦሞ እና ቡርጂ ዞኖች፤ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ምዕራብ ኦሞ፣ ቤንች ሸኮ፣ ዳዉሮ፣ ሸካ፣ ከፋ እና የኮንታ ልዩ ዞን፤ ከአፋር ክልል ዞን 2 እና 4 እንዲሁም አዲስ አበባ ላይ መደበኛና ከመደበኛ በላይ የሆነ የዝናብ መጠን ነበራቸው (ካርታ 3) ፡፡




ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et




ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 1 እስከ 10/2024
ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ




ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 1 እስከ 10/2024
ድረስ ዝናብ የዘነበባቸዉ ቀናት





ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 1 እስከ 10/2024 ድረስ የነበረዉ
የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር



ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

በሌላ በኩል በሰሜን ምዕራብ፣ ጋምቤላና በደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የቀኑ ከፍተኛ የሙቀት መጠን ከ35-41.8 ዲግሪ ሴልሽየስ ተመዝግቧል (ምስል 1) ።





ምስል 1 የቀኑ ከፍተኛ የሙቀት መጠን በዲ.ሴ

## ኢ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 1 እስከ 10/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርና ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባለፉት አስር ቀናት በደቡብ፣ በደቡብ ምዕራብ፣ በመካከለኛዉ እንዲሁም በሰሜን እና ሰሜን ምስራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች በብዙ ቦታዎቻቸዉ ላይ የተሻለ እርጥበት አግኝተዋል። ይህም ሁኔታ ለቋሚ ተክሎች የውሃ ፍላጎት መሟላት ለአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች የግጦሽ ሳርና የመጠጥ ውሃ አቅርቦትን ከማሻሻል አንፃር አዎንታዊ ሚና የነበረው ሲሆን በተለይም በደቡብ ምዕራብ፣ በመካከለኛውና በሰሜን ምስራቅ የበልግ ሰብል አምራች በሆኑት አካባቢዎች የነበረው እርጥበት የማሳ ዝግጅት ለማከናወንና የተለያዩ የበልግ ወቅት ሰብሎችን አስቀድሞ ለመዝራት የጎላ ጠቀሜታ ነበረው (ካርታ 4)፡፡




ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢ.ሜይል፡ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et




ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 1 እስከ 10/2024
ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ

## እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 1 እስከ 10/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባሳለፍነው አስር ቀናት በአብዛኛው ኦሞ ጊቤ፣ መካከለኛው እና ታችኛው ስምጥ ሸለቆ፣ መካከለኛው ምስራቃዊ አባይ፣ በላይኛው እና መካከለኛው ባሮ አኮቦ፣ በላይኛው አዋሽ እንዲሁም በጥቂት የታችኛው ምዕራባዊ ገናሌ ዳዋ ተፋሰሶች ላይ ከመጠነኛ እርጥበት እስከ ከፍተኛ እርጥበት የነበራቸው ሲሆን፤ በጥቂት የላይኛው ባሮ አኮቦ በጣም ከፍተኛ እርጥበት ተስተውሏል (ካርታ 5)፡፡




ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 1 እስከ 10/2024
ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢ.ሜይል፡ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

# እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 11 እስከ 20/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ ትንበያ

በመደበኛ ሁኔታ በፌብርዋሪ ሁለተኛ አሥር ቀናት የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች የሚጠናከሩበት ጊዜ ነው፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ፣ የመካከለኛው ኢትዮጵያና የምሥራቅ አማራ እንዲሁም የስምጥ ሸለቆ አጎራባች አካባቢዎች ዝናብ ማግኘት ይጀምራሉ፡፡


በሚቀጥሉት አሥር ቀናት ለዝናብ መፈጠር አስተዋጽኦ ሊያደርጉ የሚችሉ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ከዕለት ወደ ዕለት እየተጠናከሩ እንደሚሄድ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ በሰሜን ምስራቅ፣ በመካከለኛዉ፣ በደቡብ ምዕራብ እንዲሁም በስምጥ ሸለቆና አጎራባች አካባቢዎች የተሻለ ጥንካሬ ይኖራቸዋል፡፡ በመሆኑም፤ በመጀመሪያዎቹ አምስት ቀናቶች ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ (ካርታ 7)፡፡ በተጨማሪም አልፎ አልፎ ከሚጠናከሩት የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ላይ በመነሳት በመካከለኛዉ፣ በሰሜን ምስራቅ እና በደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ አከባቢዎች በአንዳንድ ቦታዎቻቸው ላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚያገኙ አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ ( ካርታ 6 )፡፡

በአጠቃላይ በመጪዎቹ አሥር ቀናት ከኦሮሚያ ክልል ሆሮ ጉዱር ወለጋ፣ ጅማ፣ ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ሁሉም የሸዋ ዞኖች፣ አርሲና ምዕራብና አርሲ፤ ከአማራ ክልል የደቡብ እና የሰሜን ወሎ እንዲሁም የዋግህምራ ዞኖች፣ የሰሜን ሸዋና የኦሮሚያ ልዩ ዞን፤ ከትግራይ ክልል የምስራቅ፣ የመካከለኛዉ እና የደቡብ ምስራቅ ዞኖች፤ የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች፤ የሲዳማ ክልል ዞኖች፤ አብዛኛዉ የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች፤ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ዞኖች፤ ከአፋር ክልል ዞን 4 እና 5፤ አዲስ አበባ እንዲሁም የሐረሪ እና ድሬዳዋ መደበኛና ከመደበኛ በላይ ዝናብ የሚኖራቸው ሲሆን፤ በጥቂት ስፍራዎቻቸው ላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ (ካርታ 7)፡፡ በተጨማሪም ከጋምቤላ ክልል የመዠንግ እና ጥቂት የአኝዋክ ዞኖች፤ የደቡብ ጎንደር፣ ምዕራብና ምስራቅ ጎጃም እንዲሁም የባህር ዳር ዙሪያ፤ ምዕራብና ምስራቅ ሐረርጌ፤ እንዲሁም ከሱማሌ ክልል የሲቲ እና ጥቂት የፋፈን ዞኖች ከከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው




ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

ዝናብ ያገኛሉ (ካርታ 7)። በሌላ በኩል በጋምቤላ፤ በሰሜን ምዕራብ፤ በሰሜን ምስራቅና በደቡብ ምስራቅ አከባቢዎች ላይ የቀኑ ከፍተኛ የሙቀት መጠን ከ 35 ዲግሪ ሴልሺየስ በላይ እንደሚሆን የትንበያ መረጃዎች ያሳያሉ (ካርታ 7)።




ካርታ 6 እ.ኤ.አ. ከፌብርዋሪ 11-20, 2024 የሚኖረዉ ከፍተኛ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ




ካርታ 7 እ.ኤ.አ. ከፌብርዋሪ 11-20, 2024 የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ

## እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 21 እስከ 29/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ ትንበያ


በመደበኛ ሁኔታ በፌብሪዋሪ ሦስተኛው ዘጠኝ ቀናት ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ቀስ በቀስ መደበኛ ቦታዎቻቸውን የሚይዙበትና የሚጠናከሩበት ጊዜ በመሆኑ፤ በተለይም በበልግ አብቃይ አካባቢዎች ላይ የተሻለ የደመና ሽፋንና የተስፋፋ ዝናብ መጠንና ስርጭት ይኖራል፡፡

በመጪዎቹ የመጨረሻዉ የፌብርዋሪ ዘጠኝ ቀናት በበልግ አብቃይ አካባቢዎች ላይ ማለትም በደቡብ ምስራቅ፤ ምስራቅ፤ ሰሜን ምስራቅ እንዲሁም በመካከለኛው የአገሪቱ አከባቢዎች ላይ ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ (ካርታ 8) ፡፡



ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

Rainfall performance (mm) for 21-29 Feb




ካርታ 8፡ እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 21-29፣ 2024 የሚኖረው
የዝናብ መጠን በሚ.ሜ

## እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 11 እስከ 20/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት አስር ቀናት አብዛኛዎቹ የበልግ እርጥበት ተጠቃሚና የበልግ ሰብል አብቃይ የሆኑ እንዲሁም የተለያዩ የአርብቶ አደርና የከፊል የአርብቶ አደር አካባቢዎች በተለይም በመጀመሪያዎቹ አምስት ቀናቶች ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው እርጥበት ያገኛሉ። ይህም ሁኔታ የአፈር ውስጥ እርጥበትን ስለሚያሻሽል የበልግ ወቅት አምራች የሆኑት አካባቢዎች የማሳ ዝግጅት ለማከናወንና የተለያዩ የበልግ ወቅት ሰብልችን አስቀድሞ ለመዝራት የሚያስችል በመሆኑ አርሶ አደሮች እና የሚመለከታቸው የዘርፉ አካላት አስፈላጊውን የዘር ግብዓት ከወዲሁ በማዘጋጀት የሚገኘውን ይህንን መልካም አጋጣሚ በአግባቡ ጥቅም ላይ ማዋል ያስፈልጋል፡፡ በተጨማሪም የሚገኘው እርጥበት



ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢ.ሜይል፡ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

ለቋሚ ተክሎች የውኃ ፍላጎት መሟላት ለአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች የግጦሽ ሳርና የመጠጥ ውሃ አቅርቦትን ከማሻሻል አንፃር ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡

## እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 11 እስከ 20/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ በዉሀዉ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት አስር ቀናት በአብዛኛው ኦሞጊቤ፣ የላይኛው እና የመካከለኛው ስምጥ ሸለቆ፣ አዋሽ፣ አፋር ደናክል፣ የላይኛው ባሮአኮቦ፣ የላይኛውና የመካከለኛው ምስራቃዊ አባይ፣ እንዲሁም በጥቂት የላይኛው ተከዜ፣ ገናሌ ዳዋ እና ዋቤ ሸበሌ ተፋሰሶች ላይ ከመጠነኛ እርጥበት እስከ ከፍተኛ እርጥበት መጠን እንደሚያገኙ ይጠበቃል፡፡ ይህም ሁኔታ ለገፀ ምድር እና ለከርሰ ምድር ውሃ ሀብት መሻሻል አውንታዊ አስተዋፅዎ ይኖረዋል፡፡



ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et